# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 333 መስከረም 17 2007


ግንቦት 7 ውስጥ ያለን የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ይህ ዘርፈ ብዙ ውርደት እንዲቆም ነው የምንታገለው። የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ዘመን ይህን በመሰለ ውርደት ውስጥ ሊኖር የሚገባው ህዝብ አይደለም ብለን እናምናለን። የማያቋርጠው ጥሪያችን ዛሬም ተመሳሳይ ነው። ፈልገናቸው ሳይሆን በሃይል ራሳቸውን የጫኑብንን የወያኔ ጉጅሌዎች ከጫንቃችን ላይ እናራግፋቸው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በውጭ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚያደርጉት ፀረ ወያኔ ትግል ተጠናክሮ ቀጥሏል

የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት በተንቀሳቀሱበት የአለም ዳርቻ ሁሉ በተቆጡ ኢትዮጵያውያን እየደረሰባቸው ባለው መራር ተቃውሞ ውርደትን እየተከናነቡ እንደሚገኙ ተዘግቧል። ላለፉት 23 አመታት ከአገዛዙ ጎን በመሰለፍ የኢትዮጵያን ህዝብ በመግደል፤ በማሰርና በማሰደድ የተሰማሩት እንዲሁም በተባባሪነት እየሰሩ የሚገኙት የወያኔ ሹማምንቶች ከእንግዲህ በየትኛውም የአለም ክፍል እንዳሻቸው ወጠው የሚገቡበት ሁኔታ ማክተሙን በርካታ ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን ሲናገሩ ተደምጠዋል። በቅርቡ በአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች ተካሂዶ በነበረው የጸረ ወያኔ ተቃውሞ ትዕይን የጉጅሌው ቱባ ሹማምንቶች ተዋርደውንና ተሸማቀው መሸኘታቸው የሚታወስ ሲሆን የጸረ ወያኔ ትግሉ አድማሱን በማስፋት በካናዳ እና በስዊድን የጉጅሌዎ ቱባ ሹማምንቶች ከኢትዮጵያውያን ተቃውሞ ማስተናገዳቸው ታውቋል።

በስዊድን ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በስዊድን የወያኔ ኢንባሲ አምባሳደር የሆነችውን ወ/ሮ ወይንሸት ታደሰ እና ተባባሪ ቅጥረኛ የወያኔ ሎሌዎችን በተቃውሞ አንገት ማስደፋታቸው ተዘግቧል። በተለይ አምባሳደሯ ወይንሸት ታደሰ በተቆጡት ኢትዮጵያውያን በደረሰባት ከፍተኛ ተቃውሞ በመደናገጧ ከነበረችበት መኪና አልወርድም በማለት ለረጅም ሰአታት ታግታ መቆየቷን ለማወቅ ተችሏል። በስዊድን ነዋሪ የሆኑት ኢትዮጵያኑ የተጀመረውን የወያኔ ሹማምንቶችን የማዋረድና የማሸማቀቅ እንቅስቃሴ በተጠናከረ ሁኔታ እንቀጥላለን ሲሉ ተደምጠዋል። በሌሎች የአለም አህጉራት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም የወያኔ ሹማምንቶች በሚኖሩበት ከተማ እንዳይደርሱ በማድረግ እንዲሁም በገቡበት ቦታ ሁሉ እየገቡ በማዋረድና በማሸማቀቅ እየተደረገ ባለው ጻረ ወያኔ ትግል አካል ይሆኑ ዘንድ ጥሪ ማቅረባቸውንም ለማወቅ ተችሏል። የተቃውሞ ትዕይንቱ በበርካታ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ድጋፍ እንደተቸረው ታውቋል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ወያኔ ብቻዉን በሚወዳደርበት ምርጫ ካድሬዎቹን በየመንደሩ እየላከ ምረጡኝ እያሰኘ ነዉ

በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ በመተፋቱ ጭንቀት ወስጥ የወደቀው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለምርጫ ተብየ ድራማው ድምጽ ለማሰባሰብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚኖሩ ለበርካታ አመታት በስራ አጦት የሚሰቃዩ ወጣቶችን «ስራ እንሰጣችኋለን» በሚል ሽንገላ በየቤታቸው የስራ ፈላጊዎች መለያ መታወቂያ ካርድ እያደለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ካርድ የተሰጣቸው ስራ አጥ ተብየዎቹ የመዘገቧቸው የፋሽስቱ ቅጥረኛ ካድሬዎች «ስራ እንሰጣችኋለን፤ ነገር ግን ተከታታይ ስብሰባ ስላለ ስራ ለማግኘት ስብሰባውን መሳተፍ ይጠበቅባችኋል» ሲሉ እንዳስጠነቀቋቸው በመግለፅ ሽንገላው ሆን ተብሎ ለምርጫው እየተሰራ ያለ ድራማ መሆኑን እናውቃለን ሲሉ ተናግረዋል። ተመዝጋቢዎችም በቁጣ ምርጫ ተብየ ድራማው በደረሰ ቁጥር እንደ ህፃን አንሸነገልም! በውሸት አንታለልም! መገዛት በቃን! ሲሉ በአገዛዙ ላይ መዛታቸው ታውቋል። በተለይ ቤት ለቤት እየዞሩ በመመዝገብ ላይ የሚገኙት የአገዛዙ ቅጥረኛ ካድሬዎች እየደረሰባቸው ባለው ተቃውሞ መደናገጣቸውንም ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘ ዜና ፋሽስቱ ወያኔ ለመንግስት ሰራተኞች፣ መምህራንና ተማሪዎች እየሰጠ የሚገኘው አስገዳጅ የፓለቲካ ስልጠና በተቃውሞ እየተናጠ ቀጥሏል። በተለይ ሰራተኞችና መምህራን አገዛዙ በልማት፤ በዲሞክራሲ እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ዘርፎች ላይ ይህ ነው የሚባል ስራ ባለፉት 23 አመታት ሊሰራ እንዳልቻለ አብነቶችን በማጠቃቀስ አስረድተዋል። ሙስና የአገዛዙ መለዩ መሆኑንም በማስታወስ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር የአገር ሃብት በሹማምንቶች ተዘርፎ በአገር ቤትና በውጭ ባንኮች ተከማችቶ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ከተሰብሳቢዎች የሚሰነዘረውን ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

ግዜ

## ወያኔ ጋምቤላ ዉስጥ ዜጎችን እየጨፈጨፈ ነዉ - እስከዛሬ ከ 500 በላይ ሰዎች በግፍ ተገድለዋል

ፋሽስቱ ወያኔ በጋምቤላ ክልል በመዠንግር ዞን ጎደሬ ወረዳ ከሳምንታት በፊት የጀመረው ኢትዮጵያውያንን ከአካባቢው በግፍ የማፈናቀል እና የመግደሉን ወንጀል አጠናክሮ መቀጠሉን ለማወቅ ተችሏል። የግጭቱ መንስኤ የቀድሞ የህወሐት የጦር መኮንኖችና ቱባ ሹማምንት፤ ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ከሹማምንቱ ጋር በሽርክነት የሚሰሩ ቅጥረኛ ባለሃብቶች በአካባቢው ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ተቀራምተው በመያዛቸውና የመዠንግር ጎሳ አባላትን በማፈናቀል ለከፋ ለድህነት በመዳረጋቸው መሆኑ ታውቋል። ይሁን እንጂ አሁን እየተካሄደ ላለው መጠነ ሰፊ ግድያ እንዲፈጸም ግጭቱን ከመጠንሰስ ጀምሮ የመዠንግር ጎሳ አባላትና በማደራጀትና በማስታጠቅ የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንትና ቅጥረኛ ሽርካ ባለሃብቶች ዋነኛ ተዋናይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

የፋሽስቱ ሹማምንትና ቅጥረኞች ለመዠንግር ጎሳ አባላት ለድህነታችሁ መንስኤዎች ከአማራ፤ ደቡብና ኦሮምያ ክልል የመጡት ነዋሪዎች ናቸው በማለት የተለያዩ እርምጃዎችን በነዚሁ ብሄረሰብ ተወላጆች ላይ እንዲወስዱ እያደረጉ እንደሚገኙ የአይን እማኞች ተናግረዋል። በእስካሁን የተቀናጀ ግድያ የሟቾቹ ቁጥር ከ 500 በላይ ማሻቀቡንና ከነዚህም ውስጥ በምዕራብ ጎጃም ይስማላ አካባቢ ተወላጅ የሆኑና ለረጅም ዘመናት በመዠንግር ዞን የሪ ቀበሌ ይኖሩ የነበሩ 18 የአንድ ቤተሰብ አባላቶች እንደሚገኙበት ታውቋል። በሽሽት ላይ የነበሩ 42 ሰዎች በአገዛዙ ቅጥረኛ ጦር እንዲመለሰ የተደረገ ሲሆን ከተመላሾቹ ወስጥ 40 ዎቹ ሰዎች ወዲያውኑ እንዲገደሉ መደረጉንም ለማወቅ ተችሏል። በሜጢ አዲስ ብርሃን ቀበሌም አቶ ደምለዉ ስንሻዉ፤ አቶ አያልሰዉ ደበበ እና አቶ ሙላት ቢረሳዉ የተባሉ ግለሰቦች ከነቤተሰቦቻቸዉ በእሳት ተቃጥለው የተገደሉ ሲሆን ቄስ ፈንታሁን የተባሉ ግለሰብ በገጀራ ተቆራርጠዉ ህይዎታቸዉ አልፏል፡፡ የሾኔ ቀበሌ ቤተክርስቲያንም እንዲቃጠል መደረጉን ለማወቅ ችለናል።
( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አስገዳጁ የወያኔ የፖለቲካ ስልጠና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መዉረዱ ተሰማ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በየደረጃው ለሚገኙ ተቋማት እየሰጠ የነበረውን አስገዳጅ የፖለቲካ ስልጠና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንዲቀላቀሉ ማድረጉን ተከትሎ በአገዛዙ ላይ የተለያዩ ተቃውሞዎችና ውግዘቶች እየተሰነዘሩ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። ለመጭዎቹ 3 ቀናቶች በተከታታይ ይሰጣል በተባለው በዚህ ስልጠና አገዛዙ በዋናነት ተማሪዎችን ለካድሬነት ለማዘጋጀት ያለመ እንደሆነ ተመልክቷል። ይሁን እንጂ አገዛዙ በተማሪዎች ዘንድ ተቃውሞን እያስተናገድ እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ተማሪዎቹ ምርጫ ስለደረሰ ነው ስልጠናው የሚሰጠው፣ እኛ እድሜያችን ከ18 ዓመት በታች ነው አንመርጥም፣ ለምን ትጨቀጭቁናላችሁ፣ ዘረኛው የህወሐት አገዛዝ አይመረጥም! ሲሉ መናገራቸውን ለማወቅ ተችሏል። የተማሪ ወላጆችም አገዛዙ እየወሰደ ያለውን ተማሪዎችን በገለማ የዘር ፖለቲካው የማደንቆር ተግባር በእጅጉ እንዳሳዘናቸው ሲናገሩ ተደምጠዋል። ከተማሪዎች በፊት የተደረገው የመምህራን ስልጠና ያለውጤት ከተበተነ በሁዋላ አገዛዙ አሁን ዕድሜያቸው ከ 18 አመት በታች የሆኑ ተማሪዎችን ለስልጠናው ማስገደዱን ቅሌት ነው ሲሉ መምህራን እርምጃውን ማውገዛቸው ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በአንዳንድ አካባቢዎች ተማሪዎቹ የፖለቲካ ስልጠና እንዳለ አስቀድመው በመስማታቸው፣ ከስልጠናው የቀሩ ሲሆን፣ የአገዛዙ የወረዳ ሹሞችና መምህራን ተማሪዎችን እንዲያመጡ የተለያዩ ማማለያ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ እያግባቡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በተያያዘ ዜና በአገዛዙ እየደረሰባቸው በሚገኘው ጫና በከፍተኛ ምሬት ውስጥ የሚገኙ መምህራን ስራቸውን እየለቀቁ እንደሚገኙም ታውቋል።

መስከረም 5 ይጀመራል የተባለው ትምህርት በፖለቲካ ስልጠናው የተነሳ እስከ አሁን አለመጀመሩን የተናገሩት መምህሩ በዚህ ሁኔታ በሚቀጥለው ሳምንት መደበኛው ትምህርት ይጀመራል ብለው እንደማያስቡ ተናግረዋል። በከፍተኛ ምሬት ውስጥ የሚገኙ መምህራን ስራቸውን እየለቀቁ መሆኑም አክለው ገልጸዋል ነገረ ኢትዮጵያ ዛሬ በሳራጨው ዘገባ ተማሪዎች « እኛ እድሜያችን ከ18 ዓመት በታች ነው አንመርጥም፣ ለምን ትጨቀጭቁናላችሁ፣ ኢህአዴግ አይመረጥም»የሚሉ አስተያየቶች በመስጠታቸው ፖሊስ «እየረበሻችሁ ነው» በሚል እያስፈራራቸው መሆኑን ገልጿል። የፌደራል ጉዳዩች እና የትምህርት ሚኒስቴር ባወጡት የጋራ ዕቅድ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ስልጣና የሚያስፈልገው ላልሰለጠነው የወያኔ ጉጅሌና ሎሌዎቹ ነው!

አምባገነኖች በውድም በግድም ህዝብ ሰብስባ ጠርተው ህዝቡ ፊት በቆሙ ቁጥር ሌት ከቀን የሚያባንናቸውን የተመረረ ህዝብ የነጻነት አመጽ የሚያስቀሩ ይመስላቸዋል። የህዝብ ሃብትና ጊዜ በከንቱ እንዳሻቸው እያባከኑ፣ ነጋ ጠባ ስብሰባ፣ ግምገማ፣ "ስልጠና" ወዘተ የሚጠሩት ህዝብ የነሱን ፍላጎትና ውሳኔ የኔ ነው ብሎ የሚቀበላቸው፣ የሚሰማቸው እና ፍርሃታቸውን ያቀለላቸው እየመሰላቸው ነው።

የወያኔ ጉጅሌና ሎሌዎቹ ሰሞኑን ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ሰራተኞችንና መላውን ለፍቶ አዳሪ ተሰብሰብና እናሰልጥንህ የሚሉት በአገዛዛቸው የተንገፈገፈው ህዝብ ምሬቱ ወደ አመጽ እንዳይገነፍል ያደረጉ እየመሰላቸው ነው። ዲሞክራሲንና የህዝብ ወሳኝነትና ልእልናን በተቀበሉ ሀገሮች እንደወያኔና ቀደም ብሎ እንደነበረው የደርግ ስርአት የመንግስት ስብሰባ የማይዘወተረው ለዚህ ነው። የህዝቡን ፍርድ በስብሰባ እና በስልጠና እንደማያቆሙት ስለሚያውቁ ህዝብን ስለሚያከብሩ ነው።

ሰሞኑን በመላ ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ወያኔዎች 'ስልጠና' ብለው የሚጠሩት፣ በይዘቱ አያቶቻችንን ድሮ ላውጫጪኝ ይጠቀሙበት የነበረውን አፈርሳታ የመሰለ የመደናቆሪያ ስብሰባ አላማው ግልጽ ነው።

አላማው ህዝብ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ቢቻል ለማደንዘዝ ካልተቻለም ለማስፈራራት ነው። ግፍን፣ ፍትህ ጥፋትን ልማት፣ ጭካኔን፣ ርህራሄ ለማስመሰል አፈጮሌ ነኝ ያለ ካድሬ ሁሉ የምላስ ጂምናስቲክ የሚሰራበት ጉባኤ ነው። ከተሰብሳቢው ህዝብ ከረር ያለ ጥያቄ በመጣ ቁጥር መላ ቅጡ የሚጠፋቸውም ለዚህ ነው። እነሱ የተዘጋጁት የህዝብ ጥያቄ ለመመለስ አይደለማ! የህዝቡን ጥያቄ እንደማይመልሱማ ያውቁታል።

ነገሩ መልከ ጥፉን በስም ይደገፉ ሆነና ይህንን ቧልት 'ስልጠና' ብለው ይጠሩታል። እነዚህ ራሳቸው መሰረታዊ ስልጣኔ የሌላቸው አሰልጣኞች መምህራኑን ስለትምህርት ጉዳይ ሊያሰለጥኗቸው ሲንጠራሩ አይፍሩም። ባለሙያውን ሁሉ በሙያው ካላ ሰለጠንህ ብለው ግዳጅ ስብሰባ ያጉሩታል። ይህ የወያኔ ተግባር እውቀትና ስልጣን ከተምታታባቸው የወያኔ ጉጅሌዎች ስለመጣ ብዙ ላያስገርም ይችል ይሆናል። እንደ ህዝብና እንደ ዜግነታችን ግን በያንዳንዳችን ላይ እየደረሰ ያለ ውርደት ነው። ወያኔ ካላዋረደንና ሰበአዊ ክብራችን ካላሳነሰ የሚገዛን አልመሰለውም።

ግንቦት 7 ውስጥ ያለን የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ይህ ዘርፈ ብዙ ውርደት እንዲቆም ነው የምንታገለው። የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ዘመን ይህን በመሰለ ውርደት ውስጥ ሊኖር የሚገባው ህዝብ አይደለም ብለን እናምናለን። የማያቋርጠው ጥሪያችን ዛሬም ተመሳሳይ ነው። ፈልገናቸው ሳይሆን በሃይል ራሳቸውን የጫኑብንን የወያኔ ጉጅሌዎች ከጫንቃችን ላይ እናራግፋቸው።

በአንድነት እንነሳ! በያለንበት ለዚህ ውርደት እምቢ እንበል። ውርደታችን እምቢ ያልን ቀን ይቆማል። ያን እለት ጨለማው ይገፈፋል። የነጻነታችንና የክብራችን ጎህ ይቀዳል።

በያለንበት እምቢ እንበል! ስለተገፋንና ስለተዋረድን ማመፅ መብታችን ነው። የቻልክ ተቀላቀለን። ያልተመቸህ በያለህበት በራስህ አነሳሽነት ራስህን አደራጅ። የነጻነታችን ቀን ቅርብ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !**

---

## ኢትዮጵያ ለገለልተኛ የሰብአዊ መብት መርማሪዎች በሯን እንድትከፍት አምነስቲ ኢንተርናሽናል ጠየቀ

ሲዊዘርላንድ ጄኔቫ ዉስጥ ሲካሄድ በሰነበተው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ግምገማ ላይ ተገኝቶ አቋሙን ያስታወቀው አለማቀፉ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ኢትዮጵያ ዉስጥ አገዛዙ አገሪቱ የሰአብአዊ መብት ድንጋጌዎችን እንደምታከብር ቃል መግባት ብቻ ሳይሆን፣ በተጨባጭ ገለልተኛ ወገኖች እስር ቤቶችን እንዲገበኙ፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች እንዲጎበኙና በደል የደረሰባቸውን ወገኖች ለማነጋገር መፍቀድ አለባት የሚል ጠንከር ያለ ጥጣቄ ጠየቀ። የሰብአዊ መብት ድርጅቱ ኢትዮጵያ ዉስጥ በ1992፣ 97ና 2002 እ እንደተደረገዉ ሁሉ ዘንድሮም ምርጫ እንደሚደረግ ገልጾ አገዛዙ እንደለመደዉ አሁንም በግንቦት ወር የሚካሄደዉን ምርጫ ተከትሎ ጋዜጠኞች፤ ጦማሪያንና የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች በመታሰር ላይ መሆናቸዉን ተናግሯል።

በኢትዮጵያ የጸረ ሽብርተነት ህጉ ጋዜጠኞችን፣ጦማሪዎችን፣ የሰብ ዓዊ መብት ተሙዋጋቾችን እና የተቃዋሚ ፓርቲአባሎችን ለማጥቃት እየዋለ እንደሆነ በርካታ ሪፖርቶች ደርሰውናል" ያሉት የተመድ ባለቡያዎች "ቶርቼር እና የታሰረን ሰው ማሰቃዬት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው"ብለዋል።"ሽብርተኝነትን መዋጋት መልካም ነው። ሆኖም በሽብርተኝነት ላይ የሚደረገው ሰመቻ ዓለማእፍ የሰብ ዓዊመብት ጥበቃ ጥረትን ውጤታማ ማድረግ አለበት" ያሉት ኤክስፐርቶቹ፤"የ ጸረ -ሽብር ህጉበኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ውስጥ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ሊካተት ያስፈልጋል።አላግባብ ሊገለገሉበት አይገባም"ብለዋል።

በተለይ ባለፉት ሁለት ወራት ዉስጥ ብቻ የወያኔ አገዛዝ አገር ዉስጥ የሚታተሙ አያሌ ጋዘጠችንና መጽሄቶችን ከህትመት ዉች እንዲሆኑ ማድረጉና ጋዜጠኞቹም አገር ጠለዉ እንዲሰደዱ ማድረጉ የሚታወስ ነዉ። ወያኔ እንደዚህ አይነቱን የለየለት የአፈና እርምጃ በመዉሰድ እስከዛሬ በአንድ እግሩ ቆሞ ሞት አፋፍ ላይ ሲንገዳገድ የነበረዉን የኢትዮጵያን ነጻ ሜድያ ግብዓተ መሬት ፈጽሟል። ለዚህም ይመስላል አምነስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ መንግስት ከቃል ባለፈ ተጨባጭ የሆነ የተግባር እርምጃ እንዲወስድ አለማቀፉ የሰብአዊ መብት ጉባኤግፊት ማድረግ እንደሚኖርበት መከሯል።

በኢትዮጵያ ፍትህዊ በሆነ መንገድ የመዳኘት፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ እና የመደራጀት ነጻነት በጸረ ሽብር ህጉ አማካይነት በተደጋጋሚ እየተጣሰ እንደሚገኝ የተመድ ባለሙያዎች በአጽንኦት ገልጸዋል።"በመሆኑም የ ኢትዮጵያ መንግስት በሽብርተኝነት ስም ያሰራቸውን ሰዎች እንዲፈታ ጥሪ እናቀርባለን" ያሉት የተመድ ወኪሎች፤ የታሰሩ ጋሴጠኞች፣ ጦማሪዎች፣የሰብ ዓዊ መብት ተሙዋጋቾች፣ የተቃዋሚፓርቲ መሪዎችና የሀይማኖት አባቶች ያለምንም ፍራቻና መሸማቀቅ ከጠበቆቻቸው ጋር እንዲገናኙ አሣስበዋል

## ወያኔ ጋምቤላ ዉስጥ ዜጎችን እየጨፈጨፈ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ከፋሽስቱ ወያኔ ጋር በማበር የዘር ማጥፋቱን ወንጀል በመምራት ላይ ከሚገኙት ቅጥረኛ ባለሃብቶች መካከል አቶ ገብረ መስቀል እና አቶ ማርቆስ የሚባሉ ይገኙበታል። አቶ ገብረ መስቀል የመዥንግር ተወላጆችን እንደ ወታደር በመቅጠርና በማስታጠቅ በሌሎች ብሄረሰብ ተወላጆች ላይ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረጋቸው ተረጋግጧል። ግለሰቡ ከጉጅሌው ሹማምንት አባይ ጸሃየ ጋር በሽርክነት የሚሰራ መሆኑን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በጉጅ ቀበሌ በ12 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የእርሻ ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኙ ታውቋል። ይህ የእርሻ መሬት ሰፋት በአካባቢው ለዘመናት ሰፍረው የሚኖሩት የሌላ ብሄረሰብ አባላት መሬት በጋራ ቢጨመቅም የሹማምንቱ በእጥፍ እንደሚበልጥ የአይን እማኞች አመልክተዋል።

በአካባቢው ውጥረቱ አሁንም ድረስ እንደቀጠለ መሆኑንና በአገዛዙ እንዲሁም በቅጥረኛ ባለሃብቶች መሪነት እየተፈጸመ ያለው ግድያ ተጠናክሮ መቀጠሉን ለማወቅ ተችሏል። ነዋሪዎቹም የድረሱን ጥሪ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማቅረባቸው ታውቋል። አካባቢው ከቦ የሚገኘው የፋሽስቱ ወያኔ ጦር በሚሸሹ ሰዎች ላይ እርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝም የአይን እማኞች ተናግረዋል። የዛሬ ሁለት አመት በአሜሪካ የአክላንድ የምርምት ተቋም ይፋ ያደረገው መረጃ እንዳመለከተው በጋምቤላ ክልል ከተያዙት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች መካከል ከ 70 በመቶ በላይ የሚሆኑት የተያዙት በፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንቶችና በሽርክነት በሚሰሩ ቅጥረኛ ባለሃብቶች መሆኑን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

የክልሉ ፕሬዚዳንት ግጭቱ መብረዱንና የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ወደ ቀያቸው መመለሳቸውን ቢገልጹም ፣ ዛሬ ለኢሳት የደረሰው መረጃ ግጭቱ በገጠር ቀበሌዎች ካለፉት ሁለት ቀናት ጀምሮ መቀጠሉንና በርካታ ሰዎች መሞታቸውን ያመለክታል። በአካባቢው ኢንቨስትመንት የነበራቸው 2 የቴፒ ባለሃብቶች ትናንት መገደላቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ የሞቱ በርካታ ሰዎች አሁንም ጫካ ውስጥ ተጥለው እንደሚገኙ ምንጮች ገልጸዋል። ኢሳት ከገለልተኛ ወገን ማጣራት ባይችልም፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ግን የሟቾችን ቁጥር ከመቶ በላይ ያደርሱታል። እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት በርካታ አስከሬን በየጫካው ተጥሎ ከመገኘቱም በላይ ታጣቂዎችን በመፍራት እስካሁን ለመሰብሰብ አልተቻላም።

መንግስት በቅርቡ የአካባቢውን የጸጥታ ሹም በቁጥጥሩ ስር ማዋሉ ይታወቃል። የአንዋ ሰርቫይቫል ዳይሬክተር አቶ ኒክ ኦቻላ፣ መንግስት ምርጫ ሲቀርብ ብሄረሰቦችን እርስ በርስ ማጋጨት የተለመደ ተግባሩ መሆኑን በመግለጽ ለግጭቱ መቀስቀስ መንግስትንተጠያቂ አድርገዋል። መንግስት የቀየሰው የመሬት ወረራ ፖሊስም ለግጭቱ አስተዋጽኦ ማድረጉን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። የአካባቢው ነዋሪዎች ግጭቱ በቀላሉ ይፈታል ብለው እንደማያምኑ ይናገራሉ።

# ህወሃቶች "አቅም ግንባታ" የሚሉት፤ እኛ ደግሞ "አቅም አድክም" የምንለው ሂደት

ህወሃት የመምህራንን፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችንና የመንግስት ሠራተኞችን "አቅም እገነባለው" ብሎ ተነስቷል። ለዚህ "አቅም ግንባታ" እያሉ ለሚጠሩት አሰለቺ እና አደንቋሪ አቅም አድክም ፕሮፖጋንዳ እየወጣ ያለው ወጪ ለሌላ ተግባር ውሎ ቢሆን ኑሮ የተሻለ ይሆን ነበር። የተሻለ ነገር በህወሃቶች መንደር ይሠራል ብሎ መጠበቅ ግን ሞኝነት ነው። ህወሃት የተፈጠረው አገርን ለማፍረስና ህዝብን ለማስጨነቅ እንጂ የተሻለ ሥራ ሠርቶ ህዝብን ለማስደሰት አይደለም።

ህወሃቶች በአፍቅሮተ ንዋይ አብደው አቅላቸውን የሳቱ፤ ለእውቀትና ከእነርሱ በተሻለ ደረጃ ለሚያውቅ ቅንጣትም ታክል ክብር የሌላቸው፤ ውሸት የመኖሪያቸው ድንኳን ሁኖ ለብዙ ዘመን ያኖራቸው ቡድኖች ናቸው። በዚህ ሁኔታ ራሳቸውን የገነቡ ቡድኖች የሌሎችን አቅም እንገነባለን ብለው የመነሳታቸው ነገር አገራችን የገባችበትን የውርደት አዘቀት ፍንትው አድርጎ የሚያሳየን ነው።

የንዋይ ፍቅር የክፋቶች ሁሉ መሠረት ነው። ህወሃቶች በዚህ በክፋት ሁሉ መሠረት በሆነው በንዋይ ፍቅር ያበዱ በመሆናቸው ህወሃቶችን ከክፋት፤ ክፋትን ደግሞ ከህወሃት ለይቶ ለማየት የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። እነዚህ ቡድኖች በአፍቅሮተ ነዋይ አብደው ለእብደታቸውም መድሃኒት ጠፍቶ እኛ ከሌለን አገሪቷን እንበትናታለን በሚል ቅዠት ውስጥ እንደሚኖሩም የታወቀ ነው። ህወሃቶች ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ማንኛውንም ዓይነት ወንጀል ለመፈፀም የሚያቅማሙ አይደሉም። ህዝቡን በሙሉ በገንዘብ የሚገዛ ቢያገኙ ህዝቡን በሙሉ ለመሸጥ ወደ ኋላ ይላሉ ብሎ ማሰብም አይቻልም። ይህን በመሰለ የሞራል ውድቀት ውስጥ የሚገኙ ህወሃቶች የህዝቡን አቅም እንገነባለን ሲሉ ትንሽም አለማፈራቸው አገራችን ከደረሰችባቸው የሞራል ውድቀቶች መካከል አንዱ ሁኖ ሊጠቀስ የሚችል ዓቢይ ጉዳይ ነው።

ህወሃቶች ለእውቀትና ከእነርሱ በተሻለ ደረጃ ማሰብ ለሚችል ሰው ያላቸው ጥላቻ ወደር የለውም። ለዚህም ነው ከእነርሱ መካከል ይሄ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል የተመሰገን የተማረ ሰው የማይገኘው። ለህወሃቶች የተማረ ማለት ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት እያለ ለሆዱ ያደረ እንጂ ለአገሬ፤ ለህዝቤ፤ ለወገኔ ምን በጎ ተግባር ልፈፀም የሚል አስተሳሰብ ያለው ሰው አይደለም። የህወሃቶች ዋነኛው ችግር የተማረ ሰው መጥላታቸው ብቻ ሳይሆን ሁሉንም እኛ እናውቃለን ማለታቸውም ጭምር ነው።ሁሉን እኔ አውቃለሁ ማለት ደግሞ የድንቁርና ታላቅ ምልክት ነው። ከዚህ ድንቁርና ራሱን ማላቀቅ ያልቻለ ቡድን የዜጎችን አቅም እገነባለው ብሎ መነሳቱ ከአስገራሚ በላይ ሁኖብናል።

ውሸት ጥሩ ነገር እንዳልሆነ ከህወሃቶች በቀር ሌላው ሁሉ የሚስማማበት ነገር ነው። ህወሃቶች ግን ውሸትን እንደ ታላቅ የትግል ስትራቴጂ ይቆጥሩታል።ህወሃቶች በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን በአገር ደረጃ ሲዋሹ ቅንጣት ታክል እፍረት አይሰማቸውም። እንዲያውም ውሸታቸውን እውነት እንደሆነ አድርገው ያምናሉ። ለምሳሌ ኢኮኖሚው ከ11% በላይ አድጓል ይላሉ። ይሄ አሃዝ እውነት እንዳልሆነ ይታወቃል። ህወሃቶችና የሰበሰቧቸው ኮተታም ካድሬዎች ይሄን ውሸት እውነት ነው ብለው ያምናሉ። በአጠቃላይ ህወሃቶች ስለራሳቸውም ሆነ ስለሚገዙት ህዝብ እውነቱን መናገር ሞኝነት ነው የሚል ፅኑ ዕምነት አላቸው። ይሄን ከመሰለ ፅኑ ደዌ ራሳቸውን ማላቀቅ ያልቻሉ ደካሞች የሌላውን አቅም እንገነባለን ሲሉ አለማፈራቸው ያሳፍራል።

የሰሞኑ አቅም ግንባታ ብለው የሚጠሩት ግርግር ዓላማው እና ግቡ በተሻለ ደረጃ ማሰብ የሚችሉ ዜጎች ልዩ ልዩ አማራጮችን ማየት አቁመው አካሄዳቸውን በሞራልም ሆነ በእውቀት ውዳቂ ከሆነው ከህወሃት ጋር እንዲያደርጉ ለማድረግ ነው። ብዙ ኮተታም ካድሬዎቻቸው ለራሳቸው እንኳ የማይገባቸውን አብዮታዊ ድሞክራሲ የሚባለውን ፍልስፍና አዘረክርከው ይዘው በተማሪዎችና በመምህራን ፊት ያለምንም ዕፍረት ተጎልተው እየዋሉ ነው። እነዚህ ቡድኖች ከእነርሱ በተሻለ ደረጃ የሚያስብውን ኃይል መፍራት ብቻ ሳይሆን ሥር የሠደደ ጥላቻም አላቸው። በዚህ በሚፈሩትና በሚጠሉት ዜጋ መሃል ተገኝተው ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ መስጠት ሲገባቸው ማስፈራራት ዛቻ እና ስድብን የመልሳቸው ማሳረጊያ አድርገውታል።

በመሠረቱ አቅም ግንባታ ሲባል ዜጎች ራሳቸውንም ሆነ አገራቸውን ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያደርሱ የሚችሉበትን ሁኔታ በራሳቸው ማመቻቸት የሚችሉበትን አስተሳሰብ እንዲያሳድጉ የሚያስችል ነው። አቅም የሚገነባው የዜጎችን የመጠየቅ እና የመመራመር ችሎታ አዳብሮ የተሻለ አማራጭ እንዲያፈልቁ እንጂ መንግስት የሚለውን ብቻ አምነው እንዲቀበሉ ለማድረግ አልነበረም። የህወሃቶች አቅም ግንባታ ግን  ዜጎች ማሰብ አቁመው መጠየቅንም ፈርተው ምንሊክ ቤተ-መግስት ውስጥ ከተተከሉት ዛፎች እንደ አንዱ ሁነው እንዲኖሩ ለማድረግ ነው። እነዚያ ዛፎች መጥረቢያውን ሥሎ  ሊገነድሳቸው ለሚያንዥብበው ዛፍ ቆራጭ ገንድሶ እስከሚጥላቸው ድረስ ጥላ ይሆኑታል። ያ መጥረቢያውን ስሎ የተከለላቸው ሰው ጠላታቸው መሆኑን የማወቅ አቅም ግን የላቸውም። የህወሃቶች የአቅም ግንባታ ግቡ ዜጎች እንደ ዛፉ እንዳያስቡ እና ጠላትን ከወዳጅ የሚለዩበትን  አቅም ማዳከም ነው።

ህወሃቶች ከ11% በላይ አድገናል ይላሉ። እደገቱ እውነት ከሆነ ለምን እንራባለን? ለምንስ ዜጎች ስደትን ይመርጣሉ? ለምንስ የጨው፤ የሳሙና፤ የስኳር፤ የቲማቲም እና የሽንኩርት ዋጋ የማይቀመስ ሆነ? ብሎ የሚጠይቅ ዜጋ ጠፍቶ፤ የውሸቱን የ11% እድገት  ተቀብሎ የሚኖር ዜጋ የመፍጠር ብርቱ ቅዠት አላቸው።በዚህ ቅዠት ውስጥ እንዳይኖሩ የሚያጋድቸው የለም፤ ውሸታቸውንም አምኖ መኖር የእነርሱ ችግር ነው። የእነርሱ ውሸት አምኖ መኖር አገር የሚያፍረሰው እና ዜጎችን የሚያሰጨንቀው የእኛን ውሸት እመኑ ብለው ወደ ማስገደድ ደረጃ ሲደርሱ ነው። አሁንም እያደረጉ ያሉት ይሄንኑ ነው። የመንግስት ሠራተኞች፤ መምህራንና ተማሪዎች ተገደው የህወሃቶችንን ውሸት እየተጋቱት ይገኛሉ። ኢትዮጵያዊያን ህወሃቶችን ማመን ካቆሙ ብዙ ዘመን ተቆጥሯል። ህወሃቶች በእንግሊዘኛው "ፓቶሎጂካል ላየርስ" ተብለው የታወቁ ናቸው። ይሄ ደግሞ በሽታ ነው። የህወሃቶች ውሸት ወደ በሽታ የተሸጋገረ ስለሆነ በማንኛውም መድረክና ሁኔታ የሚናገሩትን ማመን አይቻልም።ለምሳሌ የአዜብን ስታይል እንመልከት በስልክ ከጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ጋር ስትነጋገር መጀመሪያ "አዎን እኔ አዜብ ነኝ" አለች ከአንድ ደቂቃ በኋላ ተመልሳ ደግሞ "አይ እኔ አዜብ አይደለሁም" አለች። ይሄ እንግዲህ ውሸት ወደ በሽታ ተሸጋግሮባቸው የመኖሪያቸው ድንኳን መሆኑን ያሰየናል። እንግዲህ ዜጎች የህወሃቶችን ውሸት አንሰማም፤የእናንተንም አቅም ግንባታ አንፈልግም ማለት የሚችሉበት አገር የላቸውም። ዜጎች ይሄን እሰማለሁ፤ ያንን ደግሞ መስማት አልፈልግም የሚባል መብታቸው በህወሃቶች ተገፏል። ይህ የዜጎችን የመምረጥ መብት የገፈፈ ገዥ ቡድን እያደረገ ያለው የዜጎችን አቅም ማዳከም እንጂ የዜጎችን አቅም መገንባት አይደለም።አቅም በግዴታ አይገነባምና።

ህወሃቶች  የሙስና ምንጮች መሆናቸው የታወቀ ነው።ከህወሃት መንደር ከሌብነት የፀዳ ባለስልጣን አይገኝም።ሁሉም ሌቦች፤ ሁሉም ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ሰው ምን ይለኛልን የማያውቁ ናቸው። እነዚህ ቡድኖች የሚፈፅሙትን ሙስና ማስቆም አገሪቷ ከገጠሟት ፈተናዎች መካከል አንዱ ቢሆንም መቆም ይኖርበታል። ይሄን ሙስና የማስቆም ኃላፊነት ከህወሃቶች እና ከኮተታም ካደሬዎቻቸው ውጪ ያሉ ዜጎችን ሁሉ ትብብር የሚጠይቅ ነው። በዚህ ረገድ መምህራኑና ተማሪዎች ለህወሃቶች ያነሷቸው ጥያቄዎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል። ህወሃቶች በሙስና መጨማለቃቸውን ከሌቦቹ ህወሃቶች በቀር ሁሉም ያውቃል። ህወሃቶች ከእንቅልፋቸው ሲነቁ በሚሊዮን የሚቆጠር ሃብት በእጃቸው ሲገባ የትግሌ ውጤት ይላሉ እንጂ ሰርቄ ነው የሚል አስተሳሰብ በአእምሯቸው ዝር አይልም። የህወሃቶች ትልቁ ችግር የሚፈፅሙትን ዝሪፊያ ሁሉ የትግላችን ውጤት ነው ይገባናል ብለው ከልባቸው ማመናቸው ነው። በዚህ ዓይነት አስተሳሰብ የተቃኘ ቡድን የዜጎችን አቅም ለመገንባት በሚል እያካሄደ ያለው አደንቋሪ ስልጠና ተብየው የዜጎችን አቅም ያዳክም እንደሆነ እንጂ በምንም መሥፍረት የማንንም አቅም አይገነባም።

እነዚህ ቡድኖች ያለ ምንም ዕፍረት ሙስናን እንታገላለን ይላሉ። በሙስና የተጨማለቁ ባላስልጣናት ሙስናን እንዋጋለን ብለው በድፍረት ሲናገሩም ይደመጣል።በሙስና የተዘፈቁ ባላስልጣናት መኖራቸው እየታወቀ ለምን ህግ ፊት አይቀርቡም ተብለው ሲጠየቁ መልስ የላቸውም። ኢታማዦር ሹሙ ሳሞራ የኑስ ዋና ሌባ መሆኑ ይታወቃል፤ በዘረፈው የህዝብ ሃብት የባንክ ቤት ባለድርሻ እስከመሆን ደርሷል። መላኩ ፈንቴን እንዲታሠር የበየነው ህግ ሳሞራ የኑስን አይነካም። ሁሉም ኢትዮጵያዊ በህግ ፊት እኩል ነው ቢባልም ሳሞራ የኑስና መላኩ ፈንቴን እኩል የሚያይ ህግ በኢትዮጵያ የለም። በዚህ ዓይነት የሞራል ዝቅጠት ውስጥ የሚገኝ ቡድን የሚገነባው አቅም ምንድ ነው? ዜጎችን በምን አቅጣጫ ወደየት ለመውሰድ ያለመ ስልጠና ነው እየተሰጠ ያለው ተብሎ ቢጠየቅም የሚገኘው መልስ ዜጎች ሁሉ እንደ ህወሃት በጎጥ አስተሳሰብ ተተብትበው፤ ሰው ምን ይለኛል ማለትን ረስተው፤ እግዚአብሄርን መፍራት ትተው፤ ግራና ቀኝ ማየትን አቁመው ከአንድ ማሰብ ከማይችል እንስሳ ሳይለዩ እንዲኖሩ ማድረግ ነው።

የግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ህወሃት የተባለውን ዘረኛና ዘራፊ ቡድን ከተቆናጠጠበት የሥልጣን ኮርቻ ላይ አውርዶ አገሪቷን የሁሉም ለማድረግ የሚችለውን እያደረገ ነው። ለኢትዮጵያ ህዝብ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከህወሃት የበለጠ ጠላት የለም። ህወሃት ዋነኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት መሆኑ ሊሠመርበት የሚገባ ነጥብ ነው። ይሄን ጠላት ሳያቅማሙ በሁሉም መስክ መታገል ግዜው የሚጠይቀው ከዜጎች የሚጠበቅ ተግባር ነው።
ተከብሬ የምኖርበት አገር ያስፈልገኛል የሚል ሁሉ ንቅናቄያችንን እንዲቀላቀል ዛሬም ደግመን የትግል ጥሪያችንን እናቀርባለን። እኛ አገር ያሳጡንን ቡድኖች በሚገባቸው ቋንቋን ለማነጋገር ሳንቅማማ የትግሉን ባቡር ተሳፍረናል። የትግሉን ባቡር አሁኑኑ ተሳፈሩና ለሁላችንም የትሆን አገር እንፍጠር።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

## ምዕራብ አርማጭሆ ዉስጥ አስተዳዳሪዎች በሚያደርጉት ሸኩቻ ዜጎች እንደሚገደሉ ተጋለጠ

በምዕራብ አርማጮሆ ወረዳ የአብርሃጅራ ነዋሪዎች ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ በመሬት ስሪት ፣በልማትና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ ቅሬታወች ቀርበዋል፡፡በውይይቱ ላይ በመገኘት ቅሬታቸውን ያቀረቡት ነዋሪዎቹ "የወረዳው አመራሮች እርስ በርስ በመሻኮት ስልጣን ለመያዝ ሰዎችን ያስገድላሉ የበላይ አመራሮችን የኑሮ ሁኔታ በማጥናት ቤት ሰርተዋል፣ሃብት አከማችተዋል በማለት እነርሱም የበላይ አለቆቻቸውን አይነት ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ለሚያደርጉት ጥረትየሚሯሯጡ እንጅ ለሃገር ተቆርቁረው የሚሰሩ አይደሉም" ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

በእያንዳንዱ ቦታ ተገቢ የሆኑ ሰዎች አለመቀመጥም የአመራር ችግር ከመፍጠሩ ባሻገር 'ዞን መስተዳድር ላይ ዘመድ አለኝና አሾምህአለሁ ይሄን አምጣ ካልሆነም አባርርሃለሁ' ተብሎየሚፈከርበት አሰራርና የወረዳ አስተሳሰብ ባላቸው አመራሮች የሚደረግባቸው ጫና እንዳስመረራቸው ተሰብሳቢዎች ገልጸዋል፡፡ ህብረተሰቡ ኢህአዲግን እንዲጠላ የሆነበት ዋና ምክንያት አመራሩ ብቃት የሌለው ከመሆኑ በተጨማሪ በአመራር ላይ የሚያስቀምጣቸው ኃላፊዎች ሰውን በመወንጀል ፣በማሳሰርናበማስገደል የሚያምኑ በመሆኑ ህብረተሰቡ ወደ አላስፈላጊ ርምጃ የሚከት ከህብረተሰቡ ጋር በመተማመን ወደ መልካም አስተዳደር ለመውሰድ ጥረት የማያደርግ መሆኑንም የተናገሩትቅሬታ አቅራቢው ይህ ጉዳይ በጥንቃቄ ታይቶና ተገምግሞ መፍትሄ ልናገኝ ይገባናል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ቅሬታቸውን ያቀረቡት የአብርሃጅራ ነዋሪዎች ከተማዋ የወረዳ ከተማ ሆና እያለ በፕላኑ መሰረት የመኖሪያ ቤት ካርታ በማግኘት በሙብታችን ተጠቃሚ እንዳንሆን ተደርገናልበማለት ይናገራሉ፡፡ በከተማዋ ትልቁን የኗሪነት ድርሻ የያዘው ህብረተሰብ ፤በቀን ስራ ለረዢም አመት በመስራት ጥሪት የቋጠረው ክፍል ቢሆንም በሰራው ቤት ተበድሮ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለውን መብት በየጊዜው በሚደረግ የምክር ቤት ስብሰባ ተሻረ የሚል ምክንያት በመስጠት ቦታውን ለሚፈልጉት ባለሃብት በሙስና በመሰጠቱ ህብረተሰቡ በመጉላላት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡በአካባቢው የሚታረስ በብዙሽህ የሚቆጠር ትርፍ መሬት እያለ መሬት ማግኘት ያልቻሉ ከ400 በላይ ነዋሪዎች እተሰቃዩ ያሉበትን ሁኔታ በተደጋጋሚ ለአካባቢው አመራሮች ቢያሳውቁምመፍትሄ ማጣታቸውን ተናግረዋል፡፡ በአካባቢው አይገበሬ መሬት በብዛት ቢኖርም ባለሃብቶች እንደፈለጉ የሚያርሱበት ሁኔታ በግልጽ እታየ ነዋሪው ግን ተከልክሏል በማለት ቅሬታቸውንለአመራሩ አቅርበዋል፡፡

መሬት ያጡት ነዋሪዎች ለመኖር ሲሉ በኮንትሮባንድ ንግድ ተሰማርተው እንደሚገኙ የሚገልጹት ቅሬታ አቅራቢው ህብረተሰቡ ከደረሰበት እንግልትና የመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳ ወደ አመጽ በመሄድ የወረዳ አመራሩን መኪና ጠብቆ በጥይት የመታበት ሁኔታ የዚሁ ማሳያ መሆኑን ገልጸው፤አሁንም መፍትሄ በአስቸኳይ የማይሰጥ ከሆነ ሁኔታው ተባብሶ ሊቀጥል ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ መሬት እያላቸው ተጨማሪ መሬት ያገኙ የወረዳ አመራሩ ሚስጥረኞች አንዳሉ ሃገሬው የሚያውቅ ሲሆን መሬት የሚሸጡ ነጋዴዎች የተፈጠሩበት አሰራር ከጊዜ ወደጊዜ መንሰራፋቱ ያሳዘናቸው መሆኑን ተናግረው። ህጋዊ ግብር የሚከፍሉ ነዋሪዎች የሚያርሱት መሬት አጥተው በማማረር ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በውይይቱ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ የሰጡት የወረዳው አስተዳዳሪ ዋናው የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ ያለው መሬት መሆኑን አምነው ችግሩን እያባባሰው ያለው አመራሩ በኪራይ ሰብሳቢነት ዙሪያ መሰባሰቡ መሆኑን በአንክሮ ተናግረዋል፡፡ ይህም ሁኔታ አይን ያፈጠጠ ህገ ወጥ አሰራሮች እየተንሰራፋበት ያለበት መኖሩን በማመን ገልጸዋል፡፡ የወረዳው አስተዳዳሪ አክለውም በስልጣን ሽኩቻ ዙሪያ የተነሳው አስተያየትም ትክክል በመሆኑ መስተካከል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ በአይገብሬ መሬት የተወረረውን መሬት ለመቆጣጠር እንዳልቻሉ የተናገሩት አስተዳዳሪው በቀጣይ አጥንተን ርምጃ እንወስዳልን በማለት ዋናውን የህብረተሰቡ አንገብጋቢ የመሬት ጥያቄ ጉዳይ ወደጎን ገፋ ማድረጋቸው ህብረተሰቡን አሳዝኗል፡፡

የአካባቢው ህብረተሰብ መሰረታዊ ችግሮች ናቸው በማለት በዝርዝር ለከፍተኛ አመራሮች ቢያቀርቡም፤ በሽኩቻ ስልጣን ላይ ያሉት በህዝብ ፊት ጥፋተኛ እንደሆኑ እየተናገሩ ምንም አይነት እርምጃ እስካሁን አልተወሰደባቸውም፡፡ አመራሮች አሁንም ህብረተሰቡን በማንገላታት እና የራሳቸውን ጥቅም የሚገኙበትን መንገድ ይዘው በመስራት ላይ በመሆናቸው ከፍተኛ አመራሩ የመጣበት ጉዳይ ግራ አጋብቶናል፣ ማንኛውንም ማስረጃ እንስጥ እያልን ብንጠይቅም ልመናችን ወደጎን በመተው ችግሩን ሳይፈቱ መሄዳቸው አሁንም ተጋደሉ ብሎ ለህዝቡ ፈቃድ እንደመስጠት ነው በማለት የአካባበው ነዋሪዎች ለዘጋቢያችን ገልጸዋል፡፡

## በውጭ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚያደርጉት ፀረ ወያኔ ትግል . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተያያዘ ዜና የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንቶች በካናዳዋ ቶሮንቶ ከተማም በተቆጡ ኢትዮጵያውያን ከባድ ተቃውሞ እንደተደረገባቸው ታውቋል። ጉጅሌዎቹ በዘርና በኃይማኖት ከፋፍለው ሕዝብን እርስ በእርስ ለማጨራረስ፥ ኢትዮጵያን አፈራርሰው ለጥቂቶች ለማውረስ ያለሙት ከንቱ ቅዥት ሆኖ እንደቀረ በአንድነት ተባብረን በመነሳት ቶሮንቶ ላይ አሳይተናቸውል ሲሉ በጸረ ወያኔ ትግሉ የተሳተፉት ኢትዮጵያውያን መናገራቸው ተሰምቷል። በመንግሥት ስም ዙፋን ላይ ተቀምጠው የሚያስተዳድሩትን ሕዝብ በሰበብ አስባቡ እያሸበሩ፣ ኢትዮጵያውያንን በግፍ በትር እየደበደቡ፣ እያሳደዱ፣ በእስር ቤት እያሰቃዩ፣ እየገደሉና አገራችን ኢትዮጵያን እያጠፉ መሆናቸውን ጉጅሌዎቹ ያውቁታል፥ እኛም በካናዳ ምድር በምቾት ወጥተው እንዲገቡ ፍጹም አንፈቅድላቸውም ሲሉ ኢትዮጵያውያኑ መዛታቸውም ተዘግቧል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንትም ሆነ የአገዛዙ ተባባሪና ቅጥረኛ ተላላኪዎች በተገኙበት ስፍራ ሁሉ ገመናቸውን በማጋለጥ ልናዋርዳቸው፤ አንገታቸውን ልናስደፋ ይገባል ሲሉ የሚደመጡት ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያኑ ወያኔዎች ከአገራችን እስካልተወገዱ ድረስ እረፍትና ነጻነትን በውጭው ዓለም እንደማያገኙ ሊገነዘቡ ያስፈልጋል በማለት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የፀረ ወያኔ ትግሉ አካል ይሆን ዘንድ ጥሪ ማሳተላለፋቸውም ታውቋል።

## ወያኔ ብቻዉን በሚወዳደርበት ምርጫ ካድሬዎቹን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ተቃውሞም ሆነ አስተያየት መመለስ የተሳናቸው የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንቶ በዛቻና ማስፈራሪያ ቁጣውን ለማብረድ እሞከረ እንደሚገኙ ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በየ ስብሰባዎቹ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን የተመለከቱ ጥያቄዎች በተሰብሳቢዎች ዘንድ መሰንዘራቸው የታወቀ ሲሆን የወያኔ ሹማምንቶች ጥያቄዎችን አድበስብሰው ለማለፍ ሲሞክሩ ተስተውለዋል። በተደጋጋሚ ገፍተው በጠየቁ ግለሰቦች ላይ ማስፈራርያና ዛቻ እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሏል።

የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንቶች እየሰጧቸው ባላው አስገዳጅ ስልጠናዎች ላይ እየደረሰባቸው ባለው ውግዘትና ጥላቻ ግራ መጋባታቸው ታውቋል። የበላይ ቱባ ሹማምንቱ እየደረሰባቸው ላለው ውግዘቱና ጥላቻ የየክልል፤ ዞንና ወረዳ ካድሬዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ሙከራ ያደረጉ ሲሆን ጉዳዩ በየ ደረጃው ያሉ ካድሬዎችን ክፉኛ ማስቆጣቱ ታውቋል። የተፈጠረው ቅራኔ ስር መስደዱ አይቀሬ መሆኑን ያደረሰን የውስጥ ምንጫችን በተለይ በየ ደረጃው ካሉ ካድሬዎች ላይ የተፈጠረው ቅራኔ እና እየተስተዋለ ያለው የተቃውሞ ማዕበል መጭውን ጊዜ ለፋሽስቱ ወያኔ እሳት ሊያደርግበት እንደሚችል አመልክቷል።

## አስገዳጁ የወያኔ የፖለቲካ ስልጠና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መሰረት ማንኛውም የመጀመሪያ ዓመት የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነባሩ ተማሪ ከመግባቱ በፊት ከመስከረም 16 ቀን ጀምሮ ለሁለት ሳምንታት የሚቆይ ስልጠና ለመስጠት ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቆ ተማሪዎች ጥሪ እየተደረገላቸው ነው።

በሌላ ዜና በባህር ዳር ከተማ እየተሰጠ የሚገኘው የዳኞችና በህግ ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት ሰራተኞች ስልጠና በተቃውሞ እየተናጠ እንደሚገኝ የውስጥ ምንጫችን የላከልን መረጃ ያመለክታል። በፋሽስቱ ወያኔ ክልሉን እንዲመራ የተሾመው አሻንጉሊቱ ገዱ አንዳርጋቸው ስብሰባውን እየመራ እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ቅጥረኛው ገዱ በተለይ ከዳኞች እየተሰነዘረባቸው ለሚገኙት በርካታ ጥያቄዎችና የተቃውሞ አስተያየቶች መልስ ከመስጠት ይልቅ ዝምታን መርጦ እንደሚገኝ ታውቋል። ዳኞች በዳኝነት ስርዓቱ ላይ አገዛዙ እያደረገ ያለውን የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ያወገዙ ሲሆን የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ አባል እንድንሆን የሚደርስብንን ጫናና ማስፈራሪያ አሁኑኑ ያቁም ሲሉ አስጠንቅቀዋል። ይህ ካልሆነ ግን ስራ ለመልቀቅ እንደሚገደዱ መናገራቸው ታውቋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org